

“እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገረ ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ” ኤፌ4፡15

እውነት ቁ. 14

❖ የፍርድ ዓይነቶች

መመሪያችን፡-“መጽሐፍስ ምን ይላል” ? ገላ4፡30

“ከተጻፈው አትለፍ” ነቆሮ4፡6

for bible study(ለመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚዎች)የተዘጋጀ፡-

በወንድም ገረሙ ካይናታ

ጥር/7/2006 ዓ.ም

አድራሻ - ኮንሶ- ፋሻ

ስልክ- 0927070589

‹‹እኛ ግን የተሰቀለዉን ክርስቶስን እንሰብካለን ››!! ነቆሮ፩፡23

ምስጋና

ለወደደኝ ከኃጢአቴም በደሙ ላጠበኝ ለእርሱ ክብር እውል ዘንድ ከበጎ ፈቃዱና ከዘላለማዊ ሀሳቡ የተነሳ የፈጠረኝ፣ በእናቴ ማሕፀን ሳለሁ በጸጋዉ ወንጌል የጠራኝና የጠበቀኝ፣ ከምድር ማዕዘን በምህርቱ ገመድ ወደ ልጁ መንግስት የሳበኝ፣ በዉድ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የቤዛነት ሥራው በኩል እንዲያው በጸጋዉ ያጸደቀኝ፣ እውነትን እንዳውቅ ልቦናን የሰጠኝ ሕያው እግ/ርን አከብራዋለው አመልከውማለሁ::

❖ የፍርድ ዓይነቶች በመጽሐፍ ቅዱስ አንፃር

መጽሐፍ ቅዱስ አምስት የፍርድ አይነቶች እዳሉ ይናገራል እነርሱም

1. በአማኞች ኃጢአት ላይ የተደረገ ፍርድ
2. ኃጢአት በሠራ አማኝ ላይ የሚደርግ ፍርድ
3.በአማኝ ሥራ ላይ የሚደርግ ፍርድ
4.በሕይወት በሚገኙት አሕዛብ ላይ የሚደርግ ፍርድ
5.ባልዳኑ ሙታን ላይ የሚደርግ ፍርድ

- ደግሞ አንዱ ከሌለው በፍርድ ዓይነት ገፅታዎች ይለያያሉ ፡.

1.ፍርዱ የሚሰጥበት ምክንያት
2.ፍርዱ የሚሰጥበት ሰው ማንነት
3.ፍርዱ የሚሰጥበት ጊዜ
4.ፍርዱ የሚሰጥበት ቦታ
5.የፍርዱ ዓይነት
6.የፍርዱ ውጤት

1.በአማኞች ኃጢአት ላይ የተደረገ ፍርድ

1.ምክንያት ፡- በኃጢአት ምክንያት ሞትና እርግማን በሰው ሁሉ ላይ ስለ ነገሠ ሮሜ 3፡22 ሮሜ5፡ 12-21 እነዚህ ጥቅሶችን አንብብ «ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግ/ርም ክብር ጎድሎአቸዋል ፡፡ ሮሜ 3፡22

2.ፍርዱ የተሰጠበት ማንነት ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ

- ✓ እርሱ ራሱ በሥጋ ኃጢአታችን በእንጨት ላይ ተሸከመ ፡፡ 1ጴጥ2፡24 3፡18 ዕብ1፡3 2ቆሮ 5፡14-15 ኢሳ53፡4-6 ሮሜ5፡12-19 ዕብ9፡26-28 እነዚህ ጥቅሶች አንብብ

3.ጊዜ፡- ክርስቶስ በተሰቀለበት ጊዜ(በ30 ዓ.ም)

4.ቦታ፡- በግርክ ቀራኒዮ በዕብራይስጥ ጎልጎታ የሚባል ስፍራ

ኢየሱስንም ይዘው ወሰዱት መስቀልንም ተሸክሞ በዕብራይስጥ ጎልጎታ ወደ ተባለው የራስ ቅል ስፍራ ወደሚሉት ወጣ በዚያም ሰቀሉት ዮሐ19፡17 በተጨማር ሉቃ23፡32-33 ዕብ13፡11-12 ዘፀ33፡7 ያንብቡ

5.የፍርዱ ዓይነት ፡-ኃጢአት (እርግማን መሆን)

- ✓ በእንጨት የሚሰቀል የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፏልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን ። ገላ 3፡13 2ቆሮ5፡21

6.የፍርዱ ውጤት ፡- ለክርስቶስ ሞት ለአማኙ ደግሞ ጽድቅ(የዘላለም ሕይወት)

- ✓ እውነት እውነት እላችኃለሁ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም ዮሐ5፡24 በተጨማር ዮሐ3፡16-18 6፡39-40 10፡28 1ጴጥ 1፡22 2ጢሞ1፡10-11 ያንብቡ

2 ኃጢአት በሠራ አማኝ ላይ ሚደረግ ፍርድ፡፡

1.ፍርዱ የሚሰጥበት ምክንያት፡ የአማኝ የተገለጠ ኃጢአት

- ✓ የአንዳንዶች ሰዎች ኃጢአት የተገለጠ ነው ፍርድንም ያመለክታል ሌሎች ግን ይከተላቸዋል 1ጢሞ 5፡24
- ✓ ለመሆኑ አማኝ ኃጢአትን ይሰራልን ?
  ኃጢአተኛ≠ ኃጢአት የሠራ አማኝ
  ኃጢአተኛ ማለት ከኃጢአት በታች (ለኃጢአት) ተገዥ የሆነ
- ✓ ኃጢአት አይገዛችሁምና ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና ሮሜ 6፡14 1ዮሐ3፡4-10 5፡8 ከእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንደምንረዳው አማኝ ማለት ከኃጢአት ቀንበር ነጻ የወጣና ኃጢአት መሥራት ያልተፈቀደለት ሰው ማለት ነው ። ነገረ ግን ያመኑ ሰዎች ድካም ሊኖርባቸው ይችላል 2ጴጥ2፡4-10 1ዮሐ1፡8

- የጽድቅ ሰባኪ የነበረው ኖህ የወይን ጠጅ ጠጥቶ ሰክሮና በድንኳኑ ውስጥ እርቃኑን ተኝቷል ። ዘፍ9፡20-24
- በዓመጠኞች ሴሰኛ ድርጊት የተገፋውንና ጻድቅ ነፍሱን አስጨንቆ በሰዶምና ገሞራ ከተሞች የኖረው ሎጥ የወይን ጠጅ ጠጥቶ ሰክሮ ከሴት ልጆቹ ጋር የጸታ ግንኙነት አድርጓል ። ዘፍ19፡33-38
- የቆሮንቶስ ቤ/ክያን አማኞች ይህ የማይባል የሥነ ምግባር ችግር የነበርባቸው ሲሆን የችግራቸው ምንጭ በክርስቶስ ሕፃናት መሆናቸው እንደሆነ ተገልጸል ። 1ቆሮ3፡1-4

R. አማኝ ኃጢአት ቢሠራ የልጅነት መብቱ ይሰረዛል?ደግሞኃጢአት ስለ ሠራ ከእግ/ር ራሱን ማግለል ይኖርበታልን ? ፈጽሞ አይደለም የልጅነት መብቱ ሲጀመር እርሱ ለእግ/ር የተወደደ ልጁ ለመሆን መብት የሰጠውክርስቶስ ነው እንጂ በምግባር በኩል የፈፀመው

መልካም ሥራ አይደለም ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያን ለእግ/ር ያፈራው ፍሬ የማይረባ ሆኖ ቢታየውም የልጅነቱ መብቱ በዚህ የማይፈርስ መሆኑን ማሰብ ይገባዋል ። ሮሜ4፡2-6 ቲቶ3፡3-7 ኤፌ2፡8-9 ዩሐ2፡1-2 ዩሐ6፡37 10፡14 ሉቃ22፡31-32 ዕብ4፡14-16 10፡14 ያንብቡ ።

ይህ ማለት እግ/ር የልጆቹን ኃጢአት በቸልታ ይመለከታል ማለት አይደለም ። 1ዩሐ1፡5 ፍጹም ከመሆኑ የተነሳ ኃጢአትን አይቶ ቸል ማለት አይችልም ። ወደ እርሱ የሚቀርቡትም በቅድስና መቅርብ ይኖርባቸዋል ነገር ግን ቅድስናን በሰላማዊ መንገድ መለማመድ ለማይፈልጉ አማኞች እግ/ር አብዩታዊ መንገድ አለው -ቅጣት

2.ፍርዱ የሚሰጥበት ሰው ማንነት ፡- የአማኝ እኔነት (ሥጋ ላይ)

- ✓ የሚዘራ ከሥጋ መበስበስን ያጭዳልና በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለም ሕይወት ያጭዳል ገላ6፡7 1ቆሮ11፡30

3.ፍርዱ የሚሰጥበት ጊዜ፡- በማንኛውም ጊዜ

4.ፍርዱ የሚሰጥበት ቦታ ፡-በማንኛውም ቦታ

5.የፍርዱ አይነት ፡- ቅጣት(ተግሣጽ ≠ ቁጣ)

- ✓ ነገር ግን በተፈረደብን ጊዜ ከዓለም ጋር እንዳንኮነን በጌታ እንገሠጻለን ። 1ቆሮ11፡2830 ዕብ12፡5-11 2ሳሙ7፡14-15
    - ማን ይፈርዳል ? 1. አማኝ በራሱ ላይ ሮሜ13፡2 1ቆሮ11፡29-32

      2. ቤ/ክያን 1ቆሮ5፡1-5 12-13

      3. ኢየሱስ ክርስቶስ ዩሐ5፡22 ዕብ10፡30 1ቆሮ4፡4

6.የፍርዱ ውጤት ፡- ሕብረትን መመለስ 1ዩሐ 1፡3-7 1፡9 1ቆሮ7፡10

- ✓ የእምነት ሕብረት (እግ/ርን በትክክል መረዳት)
- ✓ የተግባር ሕብረት (በብርሃን መመላለስ)
    - የአማኝ ኃጢአት ከፍርድ አኳያ

1.ሞት የማይገባው (1ዩሐ5፡16)

ሰውን መበደል ፤ ራሱን መበደል

2.ሞት የሚገባው (1ዩሐ5፡17)

ቀጥታ እግ/ርን መበደል ሐዋ5፡3-5

በእግ/ር ላይ ማመጽ ዘጸ23፡20-30 ኤር7፡16 1ቆሮ11፡29-30

የእግ/ር ቁጣ በማይታዘዙ ልጆች ላይ እንጂ በሚያምኑ ልጆች ላይ አይመጣም ። ስለዚህ እግ/ር ለቁጣ አልመረጠንምና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን ለማግኘት ነው እንጂ 1ተሰ5፡9 1፡9-10 ዩሐ3፡36 ኤፌ5፡5-7

3.በአማኝ ሥራ ላይ የሚደርግ ፍርድ

- ፍርዱ የሚሰጥበት ምክንያት ፡- አማኙ በምድር ላይ ሲኖር ሕይወቱን ያነፀበት ሥራ ይፈተሻል ::

ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ቢሆን በብርም ፤ በከበረ ድንጋይም፤ በእንጨትም ፤ በሣርም ወይም በአገዳ ቢያንጽ የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል :: 1ቆሮ3፡12

- ፍርዱ የሚመለከታቸው ሰዎች ፡- በእውነት አምነው የዳኑት ሰዎች ብቻ ነው ::
  - ስለዚህ ደግሞ ብናድር ወይም ተለይተን ብንሆን እርሱን ደስ የምናሰኝ ልንሆን እናቀናልነን ::መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደርገ፤ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን ብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና :: 2ቆሮ5፡9-10 ሮሜ14፡10
  - ፍርዱ የሚሰጠው በሥራቸው ላይ እንጂ እዚህ ጋ የመዳን ወይም ያለመዳን ጥያቄ የለም ::

ፍርዱ የሚሰጥበት ጊዜ ፡- በመነጠቅ ጊዜ

- ✓ የሰው ልጅ በአባቱ ክብር ሆኖ ከመላእክቱ ጋር ይመጣል ፤በዚያን ጊዜም ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው መጠን ዋጋውን ይከፍለዋል :: ማቴ 16፡27 ሉቃ14፡14 1ቆሮ15፡22 4፡5 2ጢሞ4፡8 ራዕ22፡12

የፍርዱ አይነት ፡- በእሳት መፈተን (ሁሉን አዋቂነት)

- ✓ በእሳት ሰለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል 1ቆሮ3፡13

የፍርዱ ውጤት ፡- መልካም ሥራ የሠራ ሽልማት ሲቀበል ክፉ ሥራ የሠራ ሽልማት ይቀርበታል ::

- ✓ ማንም የገነባው ሥራ ቢጸናለት ሽልማቱን ይቀበላል ሥራ የተቃጠለበት ግን ሽልማት ይቀርበታል ፤ እርሱ ራሱ ግን ይድናል ይሁን እንጂ የሚድነው በእሳት ውስጥ በጭንቅ እንደሚያልፍ ሆኖ ነው :: 1ቆሮ3፡14-15

R. The believer has achoice of two types of building materials .

1. Eternal materials	2.Temporare materials
Gold (ወርቅ)	Wood(እንጨት)
Silver(ብር)	Hay(ሣር)
Precious stones(የከበሩ ድንጋዩች)	Straw(አገዳ)

4.በሕይወት በሚገኙት አሕዛብ ላይ የሚደርግ ፍርድ

1.ፍርዱ የሚሰጥበትምክንያት :- ክርስቶስ «ወንድሞቼ » ብሎ ለሚጠራቸው ሰዎች ያሳቡት ምህረትና ርኃራሄ ይፈተሻል

- ✓ እውነት እላቸኃለሁ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስለደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል ። ማቴ25፡40-45 ኢሳ3፡3-7 ማር9፡41

እነዚህ ወንድሞች የተባሉት የቤ/ክያን መነጠቅ ተከትሎ በሚመጣውና በጌታችን የክብር መገለጥ ወቅት « ከታላቁ መከራ » ወቅት ኢየሱስን እንደ መሢሐቸው የሚቀበሉት የአይሁድ ቅርታዎች (ከአርማጌደን ጦርነት የተረፈው አንድ ሶስተኛ የአይሁድ ሕዝብ ተብሎ ይታመናል ። ማቴ24፡21-22 ራእ7፡14 2ተስ2፡3-9 ዘካ13፡8-9

2.ፍርዱ የሚሰጥባችው ሰዎች ማንነት :- በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ ምጽአት ወቅት ከታላቁ የሰባቱ ዓመት መከራ የተረፈዉ በምድር ላይ በሕይወት የሚገኙ ነገር ግን በክርስቶስ በማመን የዘላለምን ሕይወት ያላገኙና ያልዳኑ ሰዎች ናቸው ።

- ✓ ከዓለም መጀመርያ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድርስ ያልሆነ እንግዲህም ከቶ የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆናልና ። እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበስ ሁሉ ባልዳነም ነበር ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለ ተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ ።

3.ፍርድ የሚሰጥበት ጊዜ :- በክርስቶስ የክብር መገለጥ ወቅት (ከአርማጌዶን ጦርነት በኃላና ከሺህው ዓመት መንግስት በፊት) የሚከናወን ነው ።

- ✓ የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሰን መላእክት ሁሉ በዚያን በጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል ። አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ እርሱም በጎችን ከፍየሎቹ እንደሚለይ ይለያቸዋል ።።ማቴ25፡31-32 ኢዩ3፡1-3 ማቴ13፡40-41

4.ፍርዱ የሚሰጥበት ቦታ :- በኢዩሣፍጥ ሸለቆ

- ✓ እነሆም በዚያ ወራትና በዚያ ዘመን የይሁዳንና የኢየሩሳለምን ምርኮ በምመልስበት ጊዜ አህዛብን ሁሉ ሰብስቤ ወደ ኢየሣፍጥ ሸለቆ አወርዳቸዋለሁ በዚያም ስለ ሕዝቤና ስለ ርስቴ ስለ

እስራኤል በአሕዛብ መካከል የበተኑአቸውን ምድሬንም የተካፈሉአትን እፍረድባቸዋለሁ ። ኢዩ3፡1-14 ማቴ25፡31-46 ማቴ2540-45

5.የፍርድ ዓይነት ፡- መልካም ሥራ ማድርግ ወይም አለማድርግ ማቴ25፡40-45

6.የፍርዱ ውጤት ፡- ለአንዳንዶች መዳን ሲሆን ለሌሎች መጥፋት (ማቴ25፡46)

- ✓ ለወንድሞቹ ምህርት ባደርጉት ላይ ምህረቱን በመዘረጋት ወደ አንድ ሺህ ምድራዊ መንግሥት እንዲገቡ ይፈቅደላቸዋል ።።ማቴ5፡7 ያዕ2፡13
  - ❖ ምህረትን ያገኛ ማለት ወዲያወኑ ይድናሉ ማለት አይደለም ። ይህ ከሆነ በመልካም ሥራ ወደ እግ/ር መንግሥት መግባት ይቻላል ማለት ነውን ? አይደለም ደህንነት (መዳን) በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የሆነ ነጻ ስጦታ ነው ሮሜ 3፡21-28 ። ሆኖም ወደ እግ/ር እግ/ር መንግሥት ለመግባት የተፈቀደላቸው የሺህው የሰላም መንግስት ነው ። ግን በመስሁ መንግስት ፍጻሜ ገዳማ ብዙዎች እንደሚያደርጉት ንጉሡን ይክዱታል በመስሁም ላይ ጦርነት ለመክፈት ይነሳሉ ። ራእ20፡7-10

5. ባልዳኑ ሙታን ላይ የሚደርግ ፍርድ

1.ፍርዱ የሚሰጥበት ምክንያት ፡- በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበርከኩ ዘንድ ምላስም ሁሉ ለእግ/ር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመስክር ዘንድ ነው (ፊል 2፡10-11)

2.ፍርዱ የሚሰጥበት ማንነት ፡- ያልዳኑ ሙታን

- ✓ « ባሕርም በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ » ራእ20፡13

3.ፍርዱ የሚሰጥበት ጊዜ፡- ከሺህ ዓመት መንግሥት በኃላ በተቀጠር አንድ ቀን

- ✓ የቀሩት ሙታን ግን ይህ ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድርስ በሕይወት አልኖሩም ይህ የፈተኛው ትንሳኤ ነው ..... ሺሁም ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን ከእስራት ይፈታል ። ራእ 20፡5-7 ሐዋ17፡31

4.ፍርዱ የሚሰጥበት ቦታ ፡- በታላቁ ነጭ ዙፋን ፊት (ሰማይና ምድር ያልፋሉ)

- ✓ ታላቅና ነጭ ዙፋንን በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ ስፍራም አልተገኘላቸውም ። ራእ20፡11-15

5.የፍርዱ ዓይነት ፡- ንስሐ ያልገባ ኃጢአተኛ ሊቀበል ያለው የፍርድ መጠን የሚወሰን ነው ።

- ✓ በዚያን ጊዜ የሚበዙ ተአምራት የተደረገባቸውን ከተማዎች ንስሐ ስላልገቡ ሊነቅፋቸው ጀመረ እንዲህም አለ ወዩልሽ ኮራዚ.....በፍርድ ቀን ከአንቺ ይልቅ ለስደም አገር ይቀልላታል ። ማቴ11፡20-24

6.የፍርድ ውጤት፡- ስሙ በሕይወት መጽሐፍ ተጽፏ ያልተገኘ ሁሉ ወደ እሳት ባሕር ተጣለ ። ራእ 20፡15

አመኞች ወደ ነጭ ዙፋን ፍርድ አይቀርቡም ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የኃጢአታቸውን ፍርድ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ምትክ ሆኖ ስለ ተሸከመላቸው አይፈረድባቸውም ዩሐ3፡18 5፡24 እንዲሁም በእርሱ ላይ ባላቸው እምነት ከሞት ወደ ሕይወት ስለተሻገሩ ኃጢአታቸው ዳግም አይታሰብም ሕዝ33፡16 ሚክ7፡19 ዕብ10፡14-17 ። በታላቁ የነጭ ዙፋን ፊት የሚቀርቡት ያላመኑ ፣ ኃጢአተኞች አመፀኞችና የጠፉት ብቻ ራእ 21፡8 ። ማንኛውም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ዳግም የተወለደ ሰው ሁሉ ስሙ በሕወት መጽሐፍ ውስጥ ተጽፏ። ራእ3፡5 ሉቃ10፡20 ፊል4፡3

ከዳተኞች ሰዎች ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ባለማመናቸው ምክንያት ሰማቸው ከዚህ ከሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ይደመሰሳልና የሚጠፍ ይሆናል ። መዝ69፡28 ዘፀ32፡32 ። የጠፉት ሰዎች ዕድል ፈንታ እጅግ አስደንጋጭ እንደሚሆን ቀጥሎ ባሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መረዳት እንችላለን ።።ማቴ22፡13 8፡12 13፡42 5፡25 26፡24 ማር 9፡45-48 ራዕ14፡51 19፡20

‹‹ ተፈፀመ››

ማራናታ !!

ከአዘጋጁ፡- ‹‹ አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ እንግዲያስ ሁሉ ሞቱ በሕይወትም ያሉት ስለ እነርሱ ለሞተላቸውና ለተነሣው እንጂ ወደ ፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ስለ ሁሉ ሞተ ›› 2ቆሮ5፡14-15

References

- ✓ Attonement by Derk Prince 2000-የክርስቶስ ቤዛነት
- ✓ የእምነት መሠረት By Professor Carl Fredrik
- ✓ ይህች ዓለም ምን ትሆናለች በዩአኪም ላንግሃመር
- ✓ የተሸነፈ ዓለም By Watchman nee ትርጉም ጳውሎስ ፈቃዱ
- ✓ Rightly Dividing the word of truth by C.Lscofirld

- ✓ Foundation for Righteous Living by Derk Prince
- ✓ ጠቢብ ሁን By Warren w.wiersbe ትርጉም ፈቃዱ ገብሬ